# የሙስና እና ታክስ ዳይሬክቶሬት የዜጎች ቻርተር

| ተ/ቁ | የሚቀርቡ አገልግሎቶች ጥያቄዎች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ/ የስራ ክፍል | የአገልግሎቱ አሰጣጥ ሰታንዳርድ | | | | ከተገልጋይ የሚጠበቁ ቅድመ ሁኔታዎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | የአገልግሎት ጥራት | የአገልግ ሎት ወጪ | የአገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታ | |
| 1 | የወንጀል ድርጊት ይመርመርልኝ /ይጣራልኝ/ የተመዘበረ ሀብት ይመለስልን ጥያቄ | ፧የሙስና ወንጀሎች ፧ዳይሬክቶሬት | ከባድ 2 ሰአት<br>መካከለኛ 1 ሰአት<br>ቀላል 30 ደቂቃ | 100% | በነጻ | • አቤቱታው የቀረበለት ዳይሬክቶሬት ማመልከቻውን በመመርመር ጉዳዩ ወንጀል መሆኑን ወይም ወንጀል መፈጸሙን በሚያመለክት የሰው ወይም የሰነድ ማስረጃ/ፍንጭ ሰጪ/ ማስረጃ ጋር ተሟልቶ መቅረቡ ከተረጋገጠ በኃላ ለሚመለከተው ፖሊስ እንዲያጣራ ትዕዛዝ የስተላልፋል<br>• በከባድ የሙስና ወንጀሎች ከፖሊስ ጋር በመሆን ምርመራ ያጣራል እንዲሁም ምርመራውን ይመራል፡፡<br>• - በቀረበው አቤቱታ ላይ የሙስና ወንጀል አይደለም የሚል ውሳኔ ከተሰጠ ምክንያቱን በቃል ወይም እንደ አስፈላጊነቱ በጽሁፍ ለባለጉዳዩ ይሰጣል፡፡ | ባለጉዳች/ተገልጋች ወንጀል እንዲጣራልን የሚል ማመልከቻ ወንጀል ስለመፈጸሙ የሚያመለክት/ፍንጭ የሚሰጥ/ የሰው ወይም ሰነድ ማስረጃ ካላቸውመጥቀስ የሰነድ ማስረጃ ከሆነ ማቅረብ ወይም ያለበት መጠቆም<br>- ማንነታቸውን የሚገልጽ መታወቂያ ካርድ ካላቸው ማቅረብ አለባቸው |
| 2 | በወንጀል ጉዳይ የተከፈተ መዝገብ በድርድር ይዘጋልኝ | ፧የሙስና ወንጀሎች ፧ዳይሬክቶሬት | ከ1 እስከ 2 ቀን | 100% | በነጻ | – አቤቱታው የቀረበለት ዐቃብያነ ህግ አቤቱታውን በመመርመር ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣሉ ውሳኔው አዎንታዊ ከሆነ ለሚመለከተው ዳይሬክቶሬት በእርቅ እንደተዘጋ የሚያመላክት ውሳኔ በጽሁፍ ያስተላልፋሉ፡፡ | ➢ በድርድሩ መሰረት የተካሰ ጉዳት፧የተመለሰ ሀብት |
| 3 | አለአግባብ የወንጀል ክስ ስለቀረበብኝ ክስ/ምርመራ ይነሳልኝ/ ይቋረጥልኝ ወይም ይሻሻልልኝ | ፧የሙስና ወንጀሎች ፧ዳይሬክቶሬት | ለከባድ 10 ቀን<br>ለመካከለኛ 7 ቀን<br>ለቀላል 4 ቀን | 100% | | – አለአግባብ ክስ/ምርመራ ቀረበብኝ/ተጣራብኝ የሚል ተከሳሽ አለአግባብ ክስ ቀረበብኝ የሚልባቸውን ምክንያቶች በመዘርዘር ለሚመለከተው ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፡፡<br>– አቤቱታው የቀረበለት ዳይሬክቶሬት ክሱ የሚነሳበትን ምክንያት በዝርዝር በመግለጽ ውሳኔውን ለዋና ጠቅላይ አቃቤ ሕጉ ያሳውቃል ውሳኔውም አዎንታዊ ከሆነም ክሱ እንዲነሳ ያደርጋል፡፡ ውሳኔው አሉታዊ ከሆነ ለአመልካቾች በቃል እንደ አስፈላጊነቱም በጽሁፍ ይገለጽላቸዋል፡፡ | ➢ አለአግባብ ክስ ቀረበብኝ የሚልባቸውን ምክንያቶች በመዘርዘር የክስ ቻርጅ፧እና ተያያዥ መርጃዎችን ለሚመለከተው ዳይሬክቶሬት ማቅረብ |

| ተ/ቁ | የሚቀርቡ አገልግሎቶች ጥያቄዎች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ/ የስራ ክፍል | የአገልግሎቱ አሰጣጥ ሰታንዳርድ | | | | ከተገልጋይ የሚጠበቁ ቅድመ ሁኔታዎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | የአገልግሎት ጥራት | የአገልግ ሎት ወጪ | የአገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታ | |
| 4 | አለአግባብ የተዘጋ መዝገብ ይንቀሳቀስልኝ | ፣የሙስና ወንጀሎች ፣ዳይሬክቶሬት | ከባድ 20<br><br>መካከለኛ 10<br><br>ቀላል 5 | አሰራርን ተከትሎ የተሰጠ ምላሽ | በነጻ | - የቀረበለት አካል ቅሬታውን በመመርመር ተገቢውን ውሰኔ ይሰጣል፡፡ | ➢ አለአግባብ ተዘጋብኝ የሚልባቸውን ምክንያቶች በመዘርዘር ለሚመለከተው ዳይሬክቶሬት በጽሁፍ ያቀርባል፡፡ |
| **5** | **ተከሳሽ ባለመቅረቡ (ባለመገኘቱ) የተዘጋ መዝገብ ተከሳሽ ስለተገኘ ተሰብሮ እንደገና ይከፈትልኝ** | ፣የሙስና ወንጀሎች ፣ዳይሬክቶሬት | 1 ሰዓት | ሕግና እና ተገቢውን አሰራር ተከትሎ የተሰጠ ውሳኔ፤ | በነጻ | ➢ የሚመለከተው ፖሊስ ተከሳሽ ባለመቅረቡ(ባለመገኘቱ) የተዘጋ መዝገብ ተከሳሽ ስለተገኘ ተሰብሮ እንደገና ይከፈትልኝ በማለት በክሱ ላይ የተገለፀውን ተከሳሽ በመያዝ ከፖሊስ ጣቢያው የተጻፈ ደብዳቤ በማቅረብ በአካል ይቀርባል፤<br>➢ የዳይሬክቶሬቱ ፈፃሚዎች ለፍርድ ቤት ደብዳቤ በመፃፍ መዝገቡ እንዲከፈት ያስተላልፋሉ፤<br>➢ ተከሳሽ ባለመቅረቡ(ባለመገኘቱ) የተዘጋ መዝገብ ተሰብሮ እንደገና አይከፈትም የሚል ውሳኔ የሚሰጥ ከሆነ ምክንያቱን በጽሁፍ ይገልጻል | ➢ የሚመለከተው ፖሊስ ተከሳሽ ባለመቅረቡ (ባለመገኘቱ) የተዘጋ መዝገብ ተከሳሽ ስለተገኘ ተሰብሮ እንደገና ይከፈትልኝ በማለት ተከሳሽን በመያዝ ከፖሊስ ማዕከሉ ከተጻፈ ደብዳቤ ጋር ማቅረብ አለበት |
| **6** | **ምስክር ባለመቅረቡ (ባለመገኘቱ) የተዘጋ መዝገብ ምስክር ስለተገኘ ተሰብሮ እንደገና ይከፈትልኝ** | ፣የሙስና ወን፣<br><br>ዳይሬክቶሬት | 1 ሰዓት | ሕግና እና ተገቢውን አሰራር የተከተለ ውሳኔ | በነጻ | ❖ የሚመለከተው ፖሊስ ምስክር ባለመቅረቡ (ባለመገኘቱ) የተዘጋ መዝገብ ምስክር ስለተገኘ ተሰብሮ እንደገና ይከፈትልኝ በማለት ከፖሊስ ማዕከሉ የተጻፈ ደብዳቤ ይዞ ይቀርባል፤<br>❖ የዳይሬክቶሬቱ ኃላፊዎች/ፈፃሚዎች ፖሊስ ከፖሊስ ጣቢያው የተጻፈ ደብዳቤ ይዞ መቅረቡን በማረጋገጥ ለፍርድ ቤት ደብዳቤ በመፃፍ በመዝገብ ቤት በኩል እንዲከፈት ያስተላልፋሉ፤<br>❖ መዝገቡን የመረመረው ዐቃቤ ህግ መዝገቡን እንደገና አይከፈትም የሚል ውሳኔ የሚሰጥ ከሆነ ምክንያቱን በፅሁፍ ይገልጻል፡፡ | ➢ የሚመለከተው ፖሊስ ምስክር ባለመቅረቡ (ባለመገኘቱ) የተዘጋ መዝገብ ምስክር ስለተገኘ ተሰብሮ እንደገና ይከፈትልኝ በማለት ከፖሊስ ጣቢያው የተጻፈ ደብዳቤ ማቅረብ አለበት |

| ተ/ቁ | የሚቀርቡ አገልግሎቶች ጥያቄዎች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ/ የስራ ክፍል | የአገልግሎቱ አሰጣጥ ስታንዳርድ | | | | ከተገልጋይ የሚጠበቁ ቅድመ ሁኔታዎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | የአገልግሎት ጥራት | የአገልግሎት ወጪ | የአገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታ | |
| 7 | የወንጀል ጉዳዮች ላይ መክሰስና መከራከር | ፣የሙስና ወንጀሎች ፣ዳይሬክቶሬት | ለመክሰስ-15 ቀን<br>ለክርክር- ከባድ - 4 ወር<br>መካከለኛ- 3 ወር<br>ቀላል- 2 ወር | የተከፈተ ክስ በአግባቡ የተመራ ክርክር | በነጻ | - የምርመራ መዝገብ ከፖሊስ በመረከብ በተገቢው ማስረጃ የተደገፈ መሆኑን በማረጋገጥ ለቀረበው ክስ ተገቢውን አንቀጽ በመጥቀስ ክስ በማስከፈት ተገቢውን ክርክር ማድረግ | ➢ ምርመራ ተጠናቆ ክስ ይከፈትልን የሚል አቤቱታ ለሚመለከተው ዳይሬክቶሬት ማቅረብ |
| 8 | ለይግባኝ ወይም ለሰበር ይጠየቅልኝ | ፣የሙስና ወንጀሎች ፣ዳይሬክቶሬት | ይግባኝ- 45 ቀን<br>ሰበር- 3 ወር | ሕግን ማስረጃንና ተገቢውን አሰራር ተከትሎ የተሰጠ የይግባኝ ይጠየቅልኝ አቤቱታ ውሳኔ | በነጻ | – ከፍ/ቤት የይግባኝ ወይም የውሳኔ ግልባጭ መውሰድ<br>– መዝገቡን በመመርመር ይግባኝ/ለሰበር ያስጠይቃል /አያስጠይቅም ውሳኔ መስጠት<br>– ያስጠይቀል የሚል ውሳኔ ከተሰጠ ቀሬታ/የሰበር ማመልከቻ በማዘጋጀት ለፍ/ቤት ማቅረብ እና መከራከር | ➢ መዝገቡ ውሳኔ ካገኘ ውሳኔ ያገኘበትን ቀንና የመዝገብ ቁጥሩን ካወቁት በማመልከቻው ላይ መግለጽ አለባቸው<br>➢ አቤቱታው መቅረብ ያለበት በመዝገቡ ላይ ውሳኔ ከተሰጠ በ15 ቀን ውስጥ መሆን<br>➢ አለበት ለሰበር ከሆነ ለአቃቤ ሕጉ ለሰበር ማመልከቻ ለማቅረብ የሚያስችለውን ጊዜ ታሳቢ ባደረገ መልኩ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ |
| 9 | በወንጀል ተጎጂዎች፣ጠቋሚዎችና ምስክሮች እና ከለላ ለሚጠይቁ አካላት ህጉ በሚፈቅደው መሠረት ተገቢ ጥበቃና ከለላ ማድረግ | ፣የሙስና ወንጀሎች ፣ዳይሬክቶሬት | እስከ 1 ወር | ተገቢው ምርመራ ተደርጎ ጉዳዩ በሚጠይቀው ልክ የተሰጠ ከለላ | በነጻ | - የቀረበለት አካል የከለላ ጥያቄውን በመመርመር ተገቢውን ውሰኔ ይሰጣል፡፡ | ➢ ከለላ የሚያሰጥ ስለመሆኑ የሚያስረዳ የደረሰበትን ጉዳት ወይም በደል የሚገልጽ/ፍንጭ ሰጪ/ መረጃዎችን ማቅረብ |
| 10 | የዋስትና ገንዘብ እንዲመለስልኝ ለሚመለከተው አካል ይፃፍልኝ | ፣የሙስና ወንጀሎች ፣ዳይሬክቶሬት | 3 ሰዓት | -ሕግንና ተገቢውን አሰራር ተከተሎ የተሰጠ ውሳኔ | በነጻ | - ተከሳሽ/የተከሳሽ ተወካይ የዋስትና ገንዘብ እንዲመለስልኝ በማለት በማመልከቻ ወይም በጽሕፈት ቤቱ በተዘጋጀ ፎርም ሞልተው ያቀርሉ፤<br>- የዳይሬክቶሬቱ ኃላፊዎች/ፈፃሚዎች/ ማመልከቻውን ከሚመለከተው መዝገብ ጋር በመመርመር ውሳኔ ይሰጣሉ፤<br>--ውሳኔው አሉታዊ ከሆነ ምክንያቱን በዝርዝር በመግለጽ ለባለጉዳዩ በጽሁፍ ይሰጠዋል፤ | ▪ ባለጉዳዮች/ተገልጋዮች የዋስትና ገንዘብ እንዲመለስልኝ ወይም ዋስትና እንዲነሳልኝ ለሚመለከተው አካል ይጻፍልኝ የሚል ጥያቄ በማመልከቻ ወይም በጽሕፈት ቤቱ በተዘጋጀ ፎረም ሞልተው ማቅረብ አለባቸው፤<br>▪ መዝገቡ ውሳኔ ካገኘ ውሳኔ ያገኘበትን ቀን በማመልከቻቸው መግለጽ አለባቸው፤ |
| 11 | ኤግዚቢት ይመለስልኝ | ፣የሙስና ወንጀሎች ፣ዳይሬክቶሬት | 3 ቀን | ሕግን፣ ማስረጃን እና ተገቢ አሰራር ተከትሎ የተሰጠ ውሳኔ | በነጻ | ▪ የተበዳይ ወይም የተከሳሽ ወይም ህጋዊ ተወካዮቻቸው ኤግዚቢት ይመለስልኝ የሚል ጥያቄን የሚመለከተው ዳይሬክቶሬት ማመልከቻውን በመመርመር ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል፤<br>▪ ውሳኔው አዎንታዊ ከሆነ ለሚመለከተው ፖሊስ ኤግዚቢቱ እንዲመለስ ትዕዛዝ ያስተላልፋሉ፤ ውሳኔው | ❖ ተበዳይ ወይም ተከሳሽ ወይም ተወካዮቻቸው ኤግዚቢት ይመለስልኝ የሚል ጥያቄ ለሚመለከተው ዳይሬክቶሬት ያቀርባሉ፤<br>❖ የንብረቱ ህጋዊ ባለ ንብረት መሆኑን የሚገልፅ የሰነድ ማስረጃ ካለ ማቅረብ |

| ተ/ቁ | የሚቀርቡ አገልግሎቶች ጥያቄዎች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ/ የስራ ክፍል | የአገልግሎቱ አሰጣጥ ሰታንዳርድ | | | | ከተገልጋይ የሚጠበቁ ቅድመ ሁኔታዎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | የአገልግሎት ጥራት | የአገልግ ሎት ወጪ | የአገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታ | |
| | | | | | | አሉታዊ ከሆነ ለአመልካች የጠየቀው ኤግዚቢት ለምን እንደማይመለስለት በዝርዝር በመግለፅ ምላሽ ይሰጠዋል፤ | |